# **በህጋዊ አገር ላይ የቅዠት አገር** ክፍል ፩

**አዲስ ተስፋ**

አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ እንዲሉ ወንድሞቻችን በተለይም ሰፊው የኦሮሞ ህዝብ ልክ እንደ አማራው ሁሉ ከፍተኛ የስነልበና ጦርነት የተከፈተበት እንዳይመስል ነገሮችን ሁሉ በለስላሳውና እልህ በማያጋባ መልክ እንያዛቸው በሚል ለዘብተኛ መንገድ ቢመረጥም የፈሪ ጉዞ የመሰለው ኦነግና ደጋፊዎቹ ከህግ ውጭ የሆነ ከፋፋይና ማን አለብኝነት ጦርነት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ አውጀዋል። ቀደም ሲል በተለያዩ አለማት ያሰማሯቸው የማህበራዊ ሚዲያ ወታደሮቻቸው በለው፣ አባረው፣ እረደው ዐይነት ቅስቀሳ ሲያጧጡፉ ተራ ናቸው ፣ የኦሮሞን ህዝብ አይወክሉም ወዘተ በማለት ንቀን ትተናቸው ነበር። የሚገርመው አንዳንዶቹ ይህንን የሚያደርጉት በሚኖሩበት ሃገር ህግ ከፍተኛ ወንጀል እንደሆነ እያዎቁ እንኳ ወደ ህግ እንደማናቀርባቸው እርግጠኛ ሆነው በእኩይ ተግባራቸው ቀጠሉበት። አንዳንዶችም የዩኒቨርሲቲ መምህር ሆነው እያለ ህዝብን ከህዝብ የሚያቀራርብ ፣ ሰላምና ዲሞክራሲን መስበክ ሲገባቸው ገና ለገና የሚኖሩበት አገር ህግ ዲሞክራሲ ያለገደብ በመሆንና የሚናገሩት ንግ ግር በተግባር ጉዳት ካላመጣ ተጠያቂ አለመሆናቸውን ስለሚያዉቁ በደሃ ህዝባችን ስነ ልቦና ተጫዎቱ። ሌላው በግላጭ ነፍጥ አንስቶ ኦሮሞን ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ እነጥላለሁ በማለት ከአርባ አመት በላይ ሲታገል ቆይቶ አሁን ነፍጥ በቃኝ በሰላም እታገላለሁ በማለት ወደ አገር ቤት ገባሁ ያለው ኦነግ " ትጥቅ የሚያስፈታኝ ማናባቱ ነው?" በማለት በአደባባይ በመፎከር ሲሻው ንጹሃንን በመግደል ላይ ይገኛል። ወለጋን በሙሉና ምዕራብ ሃረርጌን ፣ አርሲንና ምእራብ ሸዋ በቁጥጥሩ ስር እንደሆነም ኦፍሴልያዊ ባልሆነ መልኩ በመናገር ላይ ይገኛል። አዲስ አበባ በታሪኳ አይታው የማታውቀውን የይገባኛል ብጥብጥ እንድታስተናግድም የአንበሳውን ድርሻ ተጫውቷል። መሪው ዳወድ ኢብሳም በተለያየ ጊዜ ወደ ሚዲያ በመቅረብ የተምታታ መግለጫ በመስጠት ላይ ይገኛሉ።ዶክተር አብይ አህመድ ወደ ስልጣን በመጡበትና የአዲስ አበባ ከንቲባ የስልጣን ዘመን ስላለቀ ማን ይሾም ይሆን? በሚለው ውዝግብ ውስጥ አዲስ አበባ የእኔ ነች የሚሉ ኃይሎች ከንቲባው ኦሮሞ ካልሆነ ህዝባዊ አመጹ ይቀጥላል የሚል ማስጠንቀቂያ በመስጠታቸው ታከለ ኡማ እንዲሾሙ መደረጉን መረጃዎች ቢያመለክቱም ብዙዎቻችን ከቁም ነገር አልቆጠርነውም ነበር። ሂደቱ አላቆመም በባንዲራ ምክንያት ግጭት ተፈጠረና ፖሊስ የግጭቱን ተዋናዮች ትቶ ምንም የማያዉቁ የአዲስ አበባ ወጣቶችን ወደ እስር ቤት አጋዛቸው፤ ለዚህ አቀነባባሪዎች የኦነግ ደጋፊዎች ሲሆኑ በምትኩ የመብት ተሟጋችና ለበርካታ ፍትህ ተነፋጊዎች ጥብቅና የሚቆሙ አገር ወዳድ ሰዎች ታሰሩ። ይህ ጉዞ ወዴት እንደሚያደርሰን ሁላችንም የተረዳን አይመስለም። ይልቁንም **በህጋዊ አገር ውስጥ የቅዠት አገር መሰረቱና** አገሬን ለቀህ ውጣ ማለት ጀመሩ።የቀድሞው የኦነግ መሪና የከፋፋዩ ህገመንግስት አርቃቂ አባል( ህገመንግስት ከመሆኑ በፊት የሽግግሩ መንግስት ቻርተር አርቃቂ) ይሆኑት አቶ ሌንጮ ለታ ለፋና ብሮድካስት ሰሞኑን በሰጡት ቃለ መጠይቅ አዲስ አበባ "**የኦሮሚያ አካል ነች** "ብለዋል፤ የምናገረው አሁን ያለውን ህገ መንግስት መሰረት አድርጌ ነው። የት ቦታ ነው አዲስ አበባ የኦሮሚያ አካል እንደሆነች የተገለጸው?

በህገ መንግስቱ አንቀጽ 49 ከቁጥር 1 እስከ 5 ተዘርዝሮ እንደተገለጸው አዲስ አበባ የፌደራሉ ዋና ከተማ እንደሆነች፣ በኦሮሚያ ክልል መካከል እንድምትገኝና ተጠሪነቷም ለፌደራል መንግስቱ እንደሆነ እንጂ የኦሮሚያ ክልል አካል ነች ፈጽሞ አይልም። እንዲያውም አዲስ አበባ ከኦሮሚያ የተለየች እንደሆነች የሚያብራራው ክፍል ምናልባት ከኦሮምያ የተፈጥሮ ሃብትና አንዳንድ አቅርቦቶችን ስለምታገኝ ይህ ግንኙነት በህግ ይደነገጋል ይላል። በዚህ መሰረት አዲስ አበባም ሆነ ኦሮሚያ አንዳቸው ለሌላቸው ተመጋጋቢ ሊሆኑ እንደሚገባ እንጂ አንዳቸው በሌላው እንዲዋጡ አይናገርም። አዲስ አበባ በኦሮሚያ ክልል መሃል ነች ማለት የኦሮሚያ አካል ነች ማለት ሊሆን የሚችለው በአቶ ሌጮ ለታ አእምሮ ወይም በኦነግ ጽንፈኛ ፖለቲካ ነው።

ይህ እውነት እያለ አንድ የህዝብ ወኪል እንደሆነ የሚገልጽ ሰው እንዴት ከህግ ውጪ **አዲስ አበባ የኦሮሚያ አካል ነች** ብሎ ይናገራል? አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ እስካልሆነ ድረስ ሰውየው በዚህ ንግግራቸው ብቻ ፍርድ ቤት መቅረብ ነበረባቸው። ሌላው የአቶ ሌንጮ ለታ አስገራሚ ትእቢት የተሞላበት ደግሞም የተምታታ መልስ በበደኖ ስላለቁት አማሮች ሲጠየቁ የሰጡት መልስ ነው። ጋዜጠኛው በዚያ ጭፍጨፋ ኦንግና እርስዎ በወቅቱ እንደ

መሪነትዎ ተጠያቂ አይደላችሁም ወይ ? ብሎ ለጠየቀው ሲመልሱ አንዴ ለተፈጠረ ግድያና ወንጀል 30 አምት ሙሉ ማላዘን ምንድነው ? ማለት በሚመስል አኳኋን ዘመኔን ሁሉ ይህን ጥያቄ ስጠየቅ ስመልስ ኖሬያለሁ። ኦሮሞ ሲገደል ማንም ምንም አይልም ለእነዚህ ሰዎች ግን ይኸው ሰላሳ አመት ሙሉ ይጮሃል በማለት ወንጀለኝነታቸውን ሊያምታቱ ሞክረዋል። ምን አለበት ቢያንስ እንዚያ ስዎች መገደላቸው ትክክል አልነበረም እኔም በዎቅቱ እንደ መሪ መከላከል ባለመቻሌ ይቅርታ ቢሉና የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት እንዲያድግ ቢጥሩ። ካፈርኩ አይመልሰኝ አይነት መከላከል ብቻ ሳይሆን ለምን ለእነዚያ ለሞቱ ሰዎች ንጹሃን ሰላሳ አመት ሰው አይረሰም ብሎ መሳለቅ አሳዛኝ ብቻ ሳይሆን አስጸያፊም **ነው።ቆየት ብለው ደግሞ እኛ አልገደልነም፤ መንግስትም አልጠየቀንም በማለት አለመጠየቃቸዉን ከወንጀል ነጻ ለመሆናቸው እንደ ማስረጃ ወይም ዋስትና በማቅረብ ተከላክለዋል።**

የጉድ ቀን አይመሽም እንዲሉ ከወንጀል ነጻ የሆንኩት መንግስት ስላልጠየቀኝ ነው ይሉናል። ህብረተሰቡ ግን፣ዜጎች ግን ወንጀለኛን የማይጠይቁበት አገር መሆኑን በአግድምም ቢሆን ነግረዉናል።

ቀድሞዉኑም ቢሆን ኦነግ በኢትዮጵያ ህዝብ ልብ የለም። ለዚህም ነው በየአደባባዩ ኢትዮጵያ የምትባል አገር የለችም በማለት ብቻ ሳይሆን የመቶ አመት ታሪክ በማለት በሃገራችን ድንቅ ታሪክ ላይ የሚሳለቁት። ለነገሩ ኢትዮጵያ የለችም ቢሉም ታሪካችንን ካዱት ብንልም በሌላ መንገድ ደግሞ አማራና ትግሬ ለሶስት ሽህ ዘመናት ገዝተዋል የወደፊቱ ሶስት ሺህ ዘመን አገዛዝ ደግሞ ለእኛ በተራ ይሰጠን በማለት የህጻን ልጅ አይነት ጨዋታ ጀምረዋል። ቢሆንም ግን እየመረራቸውም እያነቃቸውም ሃገራችን ኢትዮጵያ ከሶስት ሺህ አመት የላቀ እድሜ እንዳላት በአንደበታቸውና በጽሁፎቻቸው አምነዋል።ኦነግ ራሱን በተለያየ አደረጃጀት ካዋቀረ በኋላ በተለያየ መንገድ አገሪቱን እየመራሁ ያለሁት እኔ ነኝ ማለት እንደቃጣው የምንረዳው መሪው ብቅ ብለው ትጥቅ ሊያስፈታኝ የሚችል ማንም የለም በማለት ሲያውጅ ነው። ድሃ በህልሙ ቅቤ ባይጠጣ በንጣት በሞተ ነበር እንደሚባለው ይህ ቅዠት ብቻ ነው። መቶ ሚሊየን ህዝብ ያላት አገር ከሰማንያ በላይ ነገዶች የሚገኙባት ኢትዮጵያ በአንድ የግንጠላ አጀንዳ ግማሽ ምዕተ ዐመት ታግሎ የበሬ ግንባር የማታህል ነጻ መሬት ማግኘት ያልቻለ የሽፍታ ቡድን አጋጣሚ በሰጠው ቀዳዳ ህዝብ በከፈለው ደምና አጥንት ሲያላግጥ ማየት እጅግ ያሰምማል። ኦነግ መሰረታዊ ጠላቴ አማራ ነው ቢልም እንኳ አንዱም የኢትዮጵያ ነገድ እንደማያምነው ያውቃል። ከየትኛውም የህብረተሰብ ክፍል ጋር የሚስማማ አይደለም። ሶማሊያ ጋር፣ ሲዳማ ጋር፣ ጉሙዝ ጋር፣ ጌድዮ ጋር ፣ ወላይታ ጋር ጉራጌና ሌሎችም ነገዶች ጋር በጠላትነት የተፈረጀ ብቻ ሳይሆን ሁሌም በግጭት የኖረ ሽፍታ ነው። ይህ ማለት ግን ሌሎች ነገዶች ከኦሮሞ ህዝብ ጋር ችግር አለባቸው ማለት አይደለም። ለራሱ ጥቅም የተደራጄና በሰው ደምና ህይዎት የሚነግደው ኦነግ ጋር እንጂ።

**አብሳላት** በተባለ የ አማርኛ ፊልም ታዋቂው አርቲስት ሰሎሞን ቦጋለ ልጁን በጣም የሚወድ ያለ እናት የሚያሳድግ አባት ሆኖ ይተውናል። በዚህ ፊልም አባት ልጁን በጣም ስለሚዎዳት ሃብት እያለው የፈለገችውን ማድረግ እየቻለ አጓጉል ቦታ እንደትውልና መጥፎ ልጅ እንዳትሆንበት ከመጠን ያለፈ የሚባል ባይሆንም ይቆጣጠራታል። ከእለታት አንድ ቀን ግን አንድ በጣም መጥፎ ህልም አየ። ያ ህልም በቅደም ተከተል እንዳየው በገሃዱ አለም ተፈጸመበት። ህልሙ ባይሆን ደስ ባለው ነበር፤ ነገር ግን ማስቆም አልቻለም። ስለሆነም ያለው አማራጭ ማድረግ ያለበትን ባለችው ጊዜ ማድረግ ነበር። ህልሙ እውን ሆነ ። ነገር ግን ፊልም ነው። ኦነግ እየሆነለት ያለው ህልሙ ይመስላል። እንዳሰበው እንደተመኘው ሆኖለታል። በዚያ መንግድም እየሄደ ነው። ፍጽሜው ሞት ፍጻሜው መቃብር ፍጻሜው ከኢትዮጵያውያን ልብ ብቻ ሳይሆን ከኦሮሞው ህብረተሰብ ልብም መውጣት ነው።ዶክተር ብርሃኑ የሚመሩት ግንቦት ሰባት በርካታ እንከኖችና የፕሮግራም ችግሮች ቢኖሩበትም ከፍተኛ ደጋፊውን ያጣው ግን ከኦነግ ጋር ጋብቻ በፈጸመበት ጊዜ ነበር። ይህንን ሁላችንም እናስታውሳለን። አንዲት ኢትዮጵያ የሚለው ግንቦት ሰባት ለፖለቲካ ብልጠት ቢባል እንኳ ኢትዮጵያ የምትባል አገር እድሜዋ መቶ አመት ነው ከሚል መገንጠል ጀንዳው ከሆነ ቡድን ጋር ህብረት መመስረት ራስን በራስ ማጥፋት ነበርና ይህንኑ አደረገ።

በሌላ በኩል ኦነግ ህወሃት በተዳከመ ቁጥር እንደ ህመም ማስታገሻ የሚጠቀምበት ክኒን እንደሆነም ይታወቃል። ከሁለት መጠፎዎች የተሻለዉን መጥፎ ለመምረጥ ህዝቡ እንዲጠቀምበት ያደርጋል። ኦነግ ከሚነካኝ ህውሃት ይግደለኝ እንደማለት ማለት ነው። ከሰሞኑ የምንሰማው መረጃም ወደዚህ ያደርሰናል።እንደመረጃወች ከሆነ ዶክተር ድብረጽዮን ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ **በተለይ ትምክህተኞችን** ለማንበርከክ በማለት ሲናገሩ ስንሰማ ይህንን ላለፉት ሰላሳ አመታት ሲጠቀሙበት የኖሩትን አማራን ለማሸማቀቅ የተፈጠረ ቃል መጠቀማቸው ትዝብት ነው ትርፉ እንድንል አድርጎናል።አሁን አማራ ዲሞክራቲክ ፓርቲ ብሎ ስሙን የቀየረው ሊቀመንበር አቶ ደመቀ መኮነን ከወራት በፊት ከእንግዲህ ላለፉት አማአታት ዐማራ ሲሸማቀቅባቸው የኖሩ ሆን ተብለው የተፈበርኩ ቃላት ጥቅም ላይ እንዲውሉ አንፈቅድም ብለው ነበር። ዶክተር ደብረጽዮን የስነ ልቦና ጨዋታቸውን ለመቀጠል ካልሆነ በቀር በኦነግ አማራን ማስፈራራት እንደማይችሉ ራሳቸው ያዉቁታል። አሁን አማራ እንደ በፊቱ  አገር እንዳትፈርስ ልሙት፣ ልለቅ ፣ ልደብደብ ህልውናየም ይጥፋ የሚልበት ዘመን አብቅቷልና። ከእንግዲህ አማራ የሚሞተው እየገደለ ነው። ያም ሆኖ ኦነግ የተለየ እንክብካቤ እየተደረገለት መሆኑን በድርድሩም ለእየአንዳንዱ የኦነግ ታጣቂ ቤት እንደሚሰጠው ቃል እንደተገባ  ተሰምቷል።አቦይ ስብሃት የኦነግን አርማ ይዘው እንኳን ደህና መጣችሁልን አቀባበል በመቀሌ ሲያደርጉም አይተናል። በእውነቱ ለእነኛ ፍትህን፣ እኩልነትንና ዲሞክራሲን ለማስፈን የተሰው የትግራይ ወጣቶች ደም የአቦይ ስብሃትም ሆነ የትግራይ ክልል ለኦነግ አቀባበል ያደረገው  ሽር ጉድ ክብር ሳይሆን ስድብ **ነው።የሆነው ሆነና የኦነግ ታጣቂዎች ቤት የሚሰጣቸው ስለምን ነው? ነው ወይስ የኦጋዴን ታጣቂዎች፣ የትግራይ ታጣቂዎች፣ የአማራ ታጣቂዎች፣ የሲዳማና ሌሎችም ነጻ አውጭ ብለው የታጠቁት መሳሪያ አልነበረም?**

**© አዲስ ተስፋ**

ይህ ጽሑፍ ይቀጥላል